ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካ ኤምባሲ
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
2017/32

ለበለጠ መረጃ በ011-130-7033 ይደውሉ
http://et.usembassy.gov ይጎብኙ

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (USAID) የእናቶችና ህጻናት ሞትን ለመቀነስ የሚያግዝ የ181 ሚሊዮን ዶላር መርሀ-ግብር ይፋ አደረገ

አዲስ አበባ፤ ጥቅምት 6፤2010 ዓ.ም.፤- የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (USAID) በኢትዮጵያ የእናቶችና ህጻናት ሞትን ለመቀነስ የሚያግዙ አራት መርሀ-ግብሮችን ይፋ አደረገ። እነኚህ የተሻለ ለውጥን የሚያበረታቱ መርሀ-ግብሮች፤ የኢትዮጵያ መንግሥት የእናቶች እና ህጻናትን ሞት ለመከላከል የሚያደርገውን ሁሉን አቀፍ ጥረት ይደግፋሉ። እ.አ.አ እስከ 2022 ድረስ USAID ለመርሀ-ግብሮቹ 181 ሚሊዮን ዶላር (ወደ 4.9 ቢሊዮን ብር) ወጪ የሚያደርግ ሲሆን፤የኮሪያ ዓለም አቀፍ የትብብር ድርጅት (KOICA) ለአራቱ መርሀ-ግብሮች ትግበራ ድጋፍ ያደርጋል።

አራቱ መርሀ-ግብሮች፤- የመጀመሪያ ደረጃ የህክምና ክብካቤ፤ የአዳጊ ክልሎች ጤና ስርዓት፤ የዋሽ (WASH) መርሀ-ግብር እንዲሁም የክትትል፤ ግምገማ፤ ተመክሮና ስርጸት ስራዎች ላይ ያተኩራሉ።

የለውጥ መርሀ-ግብሮቹን እውን ለማድረግ፤ በኢትዮጵያ የጤናው ዘርፍ እመርታ ለማምጣት ከተከናወኑ የጤና ዘርፍ ማሻሻያዎች፤ የእናቶች፤ የጨቅላ ህጻናት እና የቤተሰብ እቅድ አገልግሎቶች አቅርቦት፤ እንዲሁም፤ ከአቅም ግንባታ ስራዎች የተገኙ ልምዶች ተቀምረዋል።

የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ፤ የጤናውን ስርዓት የማጠናከር፤ የአገልግሎት አቅርቦትን፤ የቤተሰብና የኅብረተሰብ ጤና ልማዶችን ማጠናከር ላይ ትኩረቱን ያደርጋል። መርሀ-ግብሩ በትግራይ፤ አማራ፤ ኦሮሚያ እና ደቡብ ብሔሮች፤ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልሎች በ400 የገጠር ወረዳዎች የሚገኙ 42 ሚሊዮን ሰዎችን ተጠቃሚ ያደርጋል።

በአዳጊ ክልሎች የሚተገበረው የጤና ሥርዓት፤ ኅብረተሰቡ ጥራቱን የጠበቀ እና ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸውን የእናቶች፤ የጨቅላ ሕጻናት እና የሕጻናት ጤና አገልግሎቶችን በስፋት መጠቀም የሚያስችል ሲሆን፤ በአራቱ አዳጊ ክልሎች ማለትም፤ በአፋር፤ ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ፤ ጋምቤላ እና ሶማሌ ክልሎች ትኩረቱን አድርጓል።

ዋሽ (WASH) ለንጽህና ይበልጥ ትኩረት በመስጠት እና በቀላሉ የሚገኙ የዋሽ ምርቶችና አገልግሎቶችን ተደራሽነት በማስፋት የተቅማጥ በሽታ ስርጭትን ለመቀነስ ያለመ ነው። በአምስት ዓመቱ የትግበራ ጊዜ፤ የዋሽ መርሀ-ግብር በስምንት ክልሎች በሚገኙ 40 ወረዳዎች ከንግዱ ማኅበረሰብ አባላት ጋር በመሥራት የዋን-ዋሽ (OneWASH) አገር አቀፍ መርሀ-ግብርን የማጠናከር ስራ ይሰራል።

የክትትል፤ ግምገማ፤ ተመክሮና ስርጸት ስራዎች፤ የለውጥ መርሀ-ግብሮችን በተሻለ መንገድ ለመገንዘብ እና ለመምራት የሚያስችል ከፍተኛ ጥራት ያለው የክትትል እና ግምገማ ስርዓትን ይፈጥራል።

በመርሀ-ግብሩ መክፈቻ ስነ-ስርዓት ላይ የተገኙት በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ማይክል ሬይነር እንደገለጹት፤ “በአዲስ መልክ ይፋ የተደረጉት መርሐ-ግብሮች፤ በአርሶ አደር እና አርብቶ አደር አካባቢዎች የመጀመሪያ ደረጃ የህክምና ክብካቤ አገልግሎን ለማሻሻል፤ ንጹህ የመጠጥ ውሃ እና ንጽህና አገልግሎትን ለማስፋፋት እንዲሁም፤ ስኬቶችን ለመለካትና ለመገምገም ያግዛሉ” ብለዋል ፡፡

USAID በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የለውጥ መርሐ-ግብሩ ትግበራ እውን እንዲሆን ከፓዝ ፋይንደር ኢንተርናሽናል፤ አምረፍ፤ ፖፑሌሽን ሰርቪስ ኢንተርናሽናል፤ ዘ ሚቼል ግሩፕ እና 12 ሌሎች አጋሮች ጋር በትብብር የሚሰራ ሲሆን፤ ቁልፍ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችም የአመራር ሚና ይኖራቸዋል፡፡

***